በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ/መ/ቁ 211506

ጥቅምት 4 ቀን 2015 ዓ/ም

ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ቀነአ ቂጣታ

ፈይሳ ወርቁ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ አሱባለው

አመልካች፡- 1ኛ. አቶ ጌታሁን ታፈሰ } 1ኛ አመልካች በራሳቸው እና ለለ 2ኛ
2ኛ. አቶ አብርሃም ታፈሰ } አመልካች - ቀረቡ

ተጠሪዎች፡- 1ኛ. አቶ ዩሐንስ አፈወርቅ - ቀረቡ
2ኛ. ወ/ሮ ሰብለ አባተ } አልቀረቡም
3ኛ. ወ/ሮ ፀዳለ ሙሉጌታ }

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል።

ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የተያዘው ጉዳይ ከሳሾች እና ተከሳሽ ክርክራቸውን በእርቅ ሲቋጩ በጣልቃ ገቦች የዳኝነት ጥያቄ ላይ ውሳኔ ሳይሰጥ መታለፉን በመቃወም የቀረበ አቤቱታን የሚመለከት ነው።

ከመዝገቡ መረዳት እንደሚቻለው በፌ/መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የአሁን 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች በቀን 25/07/2012 ዓ.ም በዳፉት የተሻሻለ አቤቱታ አውራሻችን ወ/ሮ ሸታዬ ሀይሌ በቦሌ ክ/ከተማ ወረዳ 10

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የቢ/ቁ አዲስ ውስጥ ሲኖሩ በ02/12/1999 ዓ.ም በሞት ተለይተዋል፤ ሆኖም ተከሳሽ የሆነው የአሁን 1ኛ ተጠሪ ከሚች በውርስ የሚደርሰንን ይህንኑ ቤት ይዞ የሚጠቀምና በውርስ የሚደርሰንን ድርሻ በተደጋጋሚ ብንጠይቀውም ሊሰጠን ፈቃደኛ ስላልሆነ በውርስ የምናገኘው ድርሻ ተጣርቶ ድርሻችንን እንዲያካፍሰን ይወሰንልን በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡

ለክሱ ተከሳሽ መልስ እንዲሰጡ የተደረገ ሲሆን የአሁን አመልካቾችም ክርክር በተነሳበት ሀብት ላይ የውርስ ድርሻ አለን ስለሆነም የጣልቃ ገብተን እንድንከራከር በማለት አቤቱታ አቅርበዋል፡፡ የስር ፍርድ ቤት የጣልቃ ገብ አቤቱታውን እና ተያይዞ የቀረበውን ማስረጃ ተመልክቶ ከሳሽና ተከሳሽ በሚከራከሩበት ሀብት/ንብረት ላይ ጣልቃ ገቦች መብት ያላቸው መሆኑን የሚያመለክት ሆኖ እንዳገኘው በመግለፅ ጣልቃ ገብተው እንዲከራከሩ በ12/02/2012 ዓ.ም ብይን ሰጥቷል፡፡ ዋናውን ክርክር በማገድም በጣልቃ ገብ አቤቱታው ላይ ከሳሾችና ከሳሾች መልስ እንዲሰጡበት ትዕዛዝ ተሰጥቷል፡፡ በዚህ መሰረት ተከሳሽ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎች ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱ ክስ ከሰማ በኃላ የመቃወሚያ ክርክሩንና ማስረጃውን መርምሮ ታህሳስ 15/2012 ዓ.ም በዋለ ችሎት በሰጠው ብይን ጣልቃገቦች ያቀረቡት ማስረጃ ወደ ክርክሩ እንዲገቡ ለማድረግ በቂ ነው ተብሎ ታምኖበት ወደ ክርክሩ እንዲገቡ የተወሰነ መሆኑን፤ እንዲሁም አቤቱታቸው በይርጋ ያልታገደ መሆኑን በመጥቀስ በዚህ ረገድ በተከሳሽ የቀረበውን መቃወሚያ ውድቅ አድርጓል፡፡ በፍሬ ነገር ላይ ክርክር ለመስማትም ቀጠሮ ሰውጧል፡፡

በተለያየ ምክንያት ክርክር ሳይሰማ ቀጠሮ ሲለወጥ የቆየ ሲሆን ለጥቅምት 12/2013 ዓ.ም በተያዘው ቀጠሮ ከሳሾችና ተከሳሽ በሽማግሌ ተስማምተናል በማለት ስምምነታቸውን ለፍርድ ቤቱ በማቅረብ ከሳሾች ከተከሳሽ ላይ ገንዘብ የተቀበሉ መሆኑንና ክሱን ማንሳታቸውን የገለፁ ሲሆን ተከሳሽም በዕርቁ መሰረት መዝገቡ እንዲዘጋ ጠይቀዋል፡፡ ጣልቃ ገቦች በበኩላቸው ከውርስ ሃብቱ ላይ ድርሻቸውን ተከሳሽ እንዲያካፍላቸው ጠይቀው ተከሳሹም ድርሻቸውን በሽማግሌ ለመስጠት ዝግጁ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

ፍርድ ቤቱም ይህንኑ መርምሮ ህዳር 14/2013 ዓ.ም ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በሰጠው ውሳኔ ፍርድ ቤቱ የእርቅ ስምምነቱን ሲመረምር ለህግም ሆነ ለሞራል የሚቃረን ነጥብ አላገኘበትም፤ ጣ/ገቦች የእኛንም ድርሻ ተከሳሽ ሊሰጠን ይገባል በማለት የጠየቁ ቢሆንም ጣ/ገቦች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 41 መሰረት ወደ ክርክሩ እንዲገቡ የተደረገበት ምክንያት ግሬ ቀኙ በሚከራከሩበት ንብረት ላይ መብት ያላቸው በመሆኑ በክርክሩ ተካፋይ ባልሆኑበት ሁኔታ ከሳሾች ባቀረቡት ክስ መሰረት የሚሰጠው ውሳኔ ተገዢ እንዳያደርጋቸው በሚል ነው፡፡ ከሳሾች በዚህ መዝገብ ያቀረቡትን ክስ ያነሱ በመሆኑ እና ጣ/ገቦችም ቢሆኑ ከተከሳሽ የሚጠይቁት የውርስ ድርሻ ክፍፍል ጥያቄ ካላቸው ተገቢውን ዳኝነት ከፍለው ራሱን በቻለ ክስ የሚጠይቁ ከመሆኑ ውጭ በዚህ መዝገብ የሚወሰንላቸው ውሳኔ ባለመኖሩ ፍ/ቤቱ የጣ/ገቦችን ጥያቄ ባለመቀበል በቀረበው አቤቱታ መሰረት የእርቅ ስምምነቱን ተቀብሎ አጽድቋል፤ መዝገቡም በዕርቁ መሰረት ይዘጋ በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት የአሁን አመልካቾች ለከፍተኛው ፍ/ቤት ይግባኝ ቢያቀርቡም ውሳኔው የሚነቀፍበት የህግም ሆነ የፍሬ ነገር ምክንያት የለም ተብሎ ይግባኙ ተሰርዟል።

የሰበር አቤቱታው የቀረበው በዚህ ነው። አመልካች በቀን 17/03/2014 ዓ/ም ባቀረቡት የሰበር ማመልከቻ በስር ፍ/ቤት ለክሱ ምክንያት በሆነው የውርስ ሀብት ላይ አመልካቾች መብትና ጥቅም ያለን መሆኑን በማስረጃ በማስደገፍ ጣልቃ ገብተን እንድንከራከር አቤቱታ አቅርበን ጣልቃ ገብተን ፍርድ ቤቱ ሲያከራክረን ከቆየና ለውሳኔ በሚል ቀጠሮ ከተያዘ በኋላ የአሁን ተጠሪዎች ከቀጠሮ በፊት የእርቅ ስምምነት በማስገባታቸው ከሥነ ሥርዓት ህግ ውጭ የስር ከሳሽና ተከሳሽ ስለታረቁ ጣ/ገብ የሚጠይቁት የውርስ ድርሻ ክፍፍል ጥያቄ ካለ በሌላ መዝገብ እንጂ በዚህ መዝገብ የሚወሰንላቸው ውሳኔ የለም በማለት የስር ፍ/ቤት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሥነ ሥርአት ሕግ ጥሰት የተፈጸመበት ነው። በመሆኑም ተጠሪዎች ጉዳያቸውን በእርቅ የጨረሱ ስለሆነ የአሁን አመልካቾች ጥያቄ ካላቸው በሌላ መዝገብ ይጠይቁ በማለት የተሰጠው ውሳኔ ተሽሮ ግንቦት 5 ቀን 2001 ዓ.ም በጸደቀው የውርስ ሪፖርት መሰረት ተጠሪዎች ለአመልካቾች ድርሻችንን እንዲያካፍሉን እንዲወሰንልን በማለት ቅሬታቸውን አቅርበዋል።

ቅሬታው በሰበር አጣሪ ችሎት ተመርምሮ የአሁን ተጠሪዎች ጉዳያቸውን በእርቅ ስምምነት በመጨረስ መዝገብ እንዲዘጋ ሲጠይቁ የአሁን አመልካቾች (የስር ጣ/ገቦች) በጉዳዩ የእኛ መብት ስላለበት መዝገቡ ሊዘጋ አይገባም ክርክሩ ቀጥሎ ውሳኔ ይሰጥ በማለት ያቀረቡት ጥያቄ ውድቅ መደረጉ ሥነ ሥርአታዊ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት በሚል ለሰበር ችሎት እንዲቀርብና ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል።

1ኛ ተጠሪ በቀን 03/05/2014 ዓ.ም ባቀረቡት መልስ በተጠሪዎች መካከል የተደረሰው የእርቅ ስምምነት በድርሻ መብታችን ላይ ብቻ የተመሰረተ ነው፤ የድርሻ ክፍፍል ክርክሩም በእርቅ ያለቀ መሆኑና ስምምነቱም ለህግ ተቃራኒ አለመሆኑ በፍ/ቤቱ ተረጋግጦ በተመዘገበበት አስትም ሆነ ከዚያ በፊት የአሁን አመልካቾች በጣልቃ ገብነት አልተመዘገቡም፤ የስር ፍ/ቤትም በእርቅ ስምምነቱ ላይ ትእዛዝ ለመስጠት በተቀጠረበት አስት ሲቀርቡ መብታቸውን በጣልቃ ገብ አቤቱታ ያላቋቋሙ መሆኑን ከመረመረ በኋላ ከፈለጉ እንደሌሎቹ በስምምነት እንዲጨርሱ ካልፈቀዱ ደግሞ በድርሻቸው ልክ ገምተው ዳኝነት መጠየቅ እንደሚችሉ በመግለጽ ትእዛዝ ተሰጥቶ መዝገቡን መዝጋቱ ስግባብ ነው፤ ስለሆነም የአመልካቾች አቤቱታ ውድቅ እንዲደረግ በማለት ተከራክረዋል። 2ኛ እና 3ኛ ተጠሪዎች መልስ እንዲያቀርቡ ጥሪ ተደርጎ ስላልቀረቡ በፅሁፍ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል። አመልካቾች 1ኛ ተጠሪ ባቀረቡት መልስ ላይ ክርክራቸውን በማጠናከር የመልስ መልስ አቅርበዋል።

ከላይ ባጭሩ የገለፅነው የጉዳዩን አመጣጥ ነው። በበኩላችን ለሰበር ችሎቱ የተያዘውን ጭብጥ ቅሬታ ከቀረበበት ውሳኔ፤ ከግራ ቀኙ ክርክር እና ከህጉ ጋር በማያያዝ መርምረናል። የስር ፍርድ ቤት መዝገብም ቀርቦ ተመልክተናል።

እንደመረመርነው የስር ፍርድ ቤት ክርክር በተነሳበት ሀብት ላይ ድርሻ አለን ስለሆነም የጣልቃ ገብተን አንድንከራከር በማለት የአሁን አመልካቾች ያቀረቡትን አቤቱታ መርምሮ በአከራካሪው ሀብት/ንብረት ላይ መብት ያላቸው መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረባቸውን በማረጋገጥ ጣልቃ ገብተው እንዲከራከሩ ያደረገ ሲሆን የአሁን 1ኛ ተጠሪ መብት የላቸውም ጣልቃ ሊገቡ አይገባም ሚል መቃወሚያ አቅርበውም አመልካቾች ያቀረቡት ማስረጃ ወደ ክርክሩ እንዲገቡ ለማድረግ በቂ ነው ተብሎ ታምኖበት ወደ ክርክሩ እንዲገቡ የተወሰነ መሆኑን ፍርድ ቤቱ ጠቅሶ ተጠሪ ያቀረቡትን መቃወሚያም ውድቅ በማድረግ በንብረቱ ላይ መብት ያላቸው መሆኑን ማሳየታቸውን በማረጋገጥ በክርክሩ እንዲቀጥሉ አድርጓል።

ከፍሲል በተጠቀሰው መልኩ አመልካቾች 1ኛ ተጠሪ ይዘውታል በተባለው የውርስ ንብረት ላይ መብት ያላቸው መሆኑን በማስረጃቸው ማሳየታቸው በስር ፍርድ ቤት ተረጋግጧል። ይህንና ሌሎች መቃወሚያዎችን በማንሳት 1ኛ ተጠሪ የመቃወሚያ ክርክር አቅርበው በግራ ቀኑ መካከል በመቃወሚያዎቹ ላይ ዝርዝር ክርክር ከተደረገ በኃላ መቃወሚያዎቹ ከማስረጃው ጋር ተመዝነው ውድቅ ተደርገው ወደ ቀጣዩ የክርክር ስርአት ተገብቷል። አመልካቾች ጣልቃ ገብተው የጠየቁት ዳኝነትም የውርስ ድርሻቸውን ለመካፈል መሆኑን የስር ፍርድ ቤት መዝገብ ያሳያል።

የጣልቃ ገብነቱ ማመልከቻ ከፍሲል በተጠቀሰው መልኩ ከቀረበና ክርክሩም በዚህ መልኩ ከተመራ ደግሞ ከሳሽና ተከሳሽ በመካከላቸው የዕርቅ ስምምነት ማድረጋቸው በጣልቃ ገቦች የዳኝነት ጥያቄ ላይ ውሳኔ ሳይሰጥ መዝገቡን ለመዝጋት የሚያበቃ አይሆንም። በዚህ ሁኔታ ጣልቃ ገቦች በውሳኔ በሚያገኙት መብት የዳኝነት እንዲከፍሉ ሊደረጉ ከሚገባ በቀር ሌላ ክስ እንደ አዲስ የሚያቀርቡበት ወይም የጣልቃ ገብ አቤቱታው ተቀባይነት የሚያጣበት ህጋዊ ምክንያትም የለም።

በአጠቃላይ የአመልካቾች የጣልቃገብነት አቤቱታ የውርስ ድርሻቸውን የሚመለከት መሆኑ በተረጋገጠበትና የውርስ ንብረቱን ይዘዋል ከተባሉት ከ1ኛ ተጠሪ ጋር ክርክር አድርገው የተለያየ ብይን በመዝገቡ ሲሰጥ ቆይቶ ወደተከታዩ የሙግት ስርዓት ከተገባ በኃላ ይህን ሁሉ ወደጎን በማለት አመልካቾች የውርስ ድርሻ ክፍፍል ጥያቄ ካላቸው ራሱን በቻለ አዲስ ክስ የሚጠይቁ ከሚሆን በቀር በዚህ መዝገብ የሚወሰንላቸው ውሳኔ የለም ተብሎ በስር ፍርድ ቤት መዝገቡ መዘጋቱ የጣልቃገብነቱን አቤቱታ ይዘት እና የተደረገውን ክርክር እንዲሁም ክርክሩ የሚመራበትን ሥነ ሥርዓት የተከተለ ባለመሆኑ ውሳኔው መሠረታዊ

ማ ስታወሻ፦ ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ነው ብለናል፡፡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም ይህን ሳያርም ማለፉ የሚነቀፍ በመሆኑ ተከታዩን ወስነናል፡፡

ው ሣ ኔ

1. የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 79404 በቀን 14/03/2006 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 268929 በቀን 24/09/2013 ዓ.ም ያሳለፈው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሻሽሏል፡፡

2. አመልካቾች ራሱን በቻለ አዲስ ክስ ከሚጠይቁ በቀር ክርክር በተደረገበት መዝገብ የሚወሰንላቸው ውሳኔ የለም ተብሎ የተሰጠው የውሳኔ ክፍል ተሽሯል፡፡

3. የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት የተዘጋውን መዝገብ በማንቀሳቀስ ክርክሩን ከቆመበት ቀጥሎ በአመልካቾች የዳኝነት ጥያቄ ላይ ተገቢውን እንዲወስን ጉዳዩን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 341(1) መሰረት መልሰናል፡፡ የውሳኔው ግልባጭ ይድረሰው፡፡

4. በተጠሪዎች መካከል የተደረገውን የእርቅ ስምምነት የስር ፍርድ ቤት ተቀብሎ ያሳለፈው ትዕዛዝ የፀና ነው ብለናል፡፡

5. የስር ፍርድ ቤት መዝገብ በመጣበት መልኩ ይመለስ፡፡

6. ግራ ቀኙ ወጪና ኪሣራ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መ/ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ሰ/ፕ

ማ ስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም